homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ውድ ነዋሪ

**በታላቁ የቤቶች ግንባታ እና በሰማይ-ጠቀስ ፎቆች መልሶ ማልማት ላይ ወቅታዊ መረጃ**

ሆምስ ቪክቶሪያ ስለ ታላቁ የቤቶች ግንባታ ሂደት እና የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች መልሶ ማልማት መርሃ ግብር እርስዎን ለማሳወቅ ነው እየጻፈ ያለው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 ሰፈሮች ወይም ሳበርቦች ውስጥ ለሚኖሩ የአሁን እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ቤቶችን እያቀረብን ነው።

**የዛሬው ማስታወቂያ በቤትዎ ወይም በሕንጻዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፡-

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

በእነዚህ አዳዲስ ሕንፃዎች ውስጥ ካሉ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እንገናኛለን ። ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣ መልሶ ማልማት በመካሄድ ላይ እያለ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## በአቅራቢያዎ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

እነዚህን ነዋሪዎች የመዛወሪያ አማራጮችን ለመደገፍ አዳዲስ ቤቶች በአቅራቢያው በመሰራት ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፕራሃን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ
- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ እክል ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ እንዲሁም የህዝብ ማመላለሻ በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም በነዚህ ቤቶች ደህንነትን፣ ብርሃንን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች አብረው ይኖራሉ።

## በሌሎች ቦታዎች ምን እየሆነ ነው?

በ**ካርልተን በሊጊን እና ኒኮልሰን ስትሪቶች**፣ የአዳዲስ ቤቶች ዕቅዶች በነዋሪዎች ግብአት ይመራሉ። በ2031 248 በጥሩ ሁኔታ በተዘጋጀ ሰፈር ውስጥ የተሰሩ አዳዲስ ቤቶችን ለማድረስ የማፍረስ ሥራ በመካሄድ ላይ ነው።

በ**ፍሌሚንግተን እና በኖርዝ ሜልበርን** የሚገኙት የቀሩት ቤተሰቦች ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ድጋፍ እየተሰጠ ነው። የድሮ ሕንፃዎች ማፍረስ ለመጀመር ስንዘጋጅ፣ የነዋሪዎችን አስተያየት እና በአዲሶቹ ቤቶች ውስጥ ምን ማየት እንደሚፈልጉ እያጤንን ነው።

በ**ሳውዝ ያራ እና ሪችመንድ** የሚኖሩ የሚዛወሩ ነዋሪዎችን መዛወራቸው ቀጥለዋል እና ብዙ አባወራዎች በአቅራቢያው ወደሚገኙ አዳዲስ ቤቶች ተዛውረዋል። ከ85% በላይ የሚሆኑ አባወራዎች ተዛውረዋል፣ ወይም በመዛወር ላይ ናቸው፣ እና ሁሉም እስከ የካቲት 2026 ለመዛወር በሂደት ላይ ናቸው።

## ወቅታዊ መረጃ ያግኙ፣ ከኛ ጋር መገናኘትዎም አያቋርጡ

በቋንቋዎ ጨምሮ ስለ መልሶ ማልማት መርሃ ግብር መረጃ ለማግኘት homes.vic.gov.au መጎብኘት ይችላሉ።

መደበኛ ወቅታዊ እና አዲስ መረጃዎች ለማግኘት በመመዝገብ ግንኙነትዎን መቀጠል ይችላሉ።

ድህረ ገጹን እንዲጎበኙ፣ ከአካባቢዎ የቤቶች ቢሮ ጋር እንዲነጋገሩ፣ በመረጃ ክፍለ ጊዜዎች ላይ እንዲገኙ እና ከእኛ ጋር ግንኙነትዎን እንዲቀጥሉ እናበረታታዎታለን።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026